ታላቅ የስብሰባ ጥሪ

ግንቦት7 ንቅናቄ የተፈጠረው የ1997 አ.ም የግንቦት ሰባት ምርጫና ከእዚህ ምርጫ በኋላ በሃገራችን ውስጥ የተከሰተውን ሁኔታ በሚገባ በመገምገም ነው፡፡ ይህ ግምገማ በአጭሩ እንዲህ ይላል፡፡

ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ስርአተ መንግስት ለመቆም የሚያስችል የፖለቲካ ብስለት አለው፡፡
ተቃዋሚ ድርጅቶችም በሰለጡን መንገድ ተወዳድረው ስልጣን መያዝ ይችላሉ፡፡
በግንቦቱ ምርጫ የወያኔ ኢህዴግ አገዛዝ በህዝብ ድምጽ ተሸንፏል፡፡
ወያኔ ግን ሽንፈቱን አልቀበልም ብሏል፡፡
ዜጎችን አሳዷል ቀጥቅጧል አሰሯል ገድሏል፡፡
የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችን ጋዜጠኞችን የህዝብ መብት ተሟጋቾችን ወህኒ ወርውሯል፡፡ ድርጅታቸውን አፍርሷል፡፡
የግንቦት 1997 ምርጫ እንደማይደገም በቃልም በድርጊትም አረጋግጧል፡፡
ሁሉንም ሰብአዊ መብቶች ገፏል፡፡ የሃገሪቱን ሃብት ዘረኛ በሆነ መንገድ ለተደራጁ በወያኔ ኢህአዴግ በሚመሩ ኩባንያዎች እጅ ማሰባሰቡን ቀጥሏል፡፡ ሰራዊቱንና ደህንነቱን ከመቼውም በከፋ መልኩ ዘረኛ በሆነ መንገድ አዋቅሯል፡፡
ስልጣን ላይ ለመሰንበት የሃገር ድንበር ቆርሶ ሰጥቷል፡፡ የጎረቤት ሃገር ወሯል፡፡ ሃገራዊ ክህደት ፈጽሟል፡፡
ከጥፋት እንዲመለስ ተመክሯል፡፡ ተለምኗል፡፡ ምላሹ ተጨማሪ እብሪት ንቀትና ብልግና ሆኗል፡፡
ግንቦት7 የተቋቋመው እንዲህ አይነቱን የአገዛዙን እብሪት እንዴት እንቋቋማለን የሚል ጥያቄ አንስቶ መልስ ከሰጠ በኋላ ነው፡፡

ግንቦት7 ወያኔ የሰለጠነ ፖለቲካ የማይገባው ድፍን ነገር በመሆኑ፣ እስኪገባው መቀጥቀጥ ወይም መወገድ ይኖርበታል ብሎ ያምናል፡፡

ግንቦት7 ወያኔ ኢህአዴግ በሃገራችንና በሁላችንም ላይ እየፈጸመ ያለው አዋራጅ ድርጊት እንዲቆም ሰፊ ህዝባዊና ደርጅታዊ ህብረት መፍጠር ተገቢ ነው ይላል፣ ይቻላልም ብሎ ያምናል፡፡

ግንቦት 7 ወያኔ ኢህአዴግ አልበርድ ባለው ጥጋቡ እራሱን አሳብጦ መውጣት ከማይችልበት የቀውስ አዘቅት ውስጥ ተደፍቋል የሚል እምነት አለው፡፡

በአሃው ልክ የወያኔ/ኢህአዴግን እብሪት ተንኮል የድርጅት የገንዘብ የብቃትና አቅም ማምከን የሚችል ተቃዋሚ ሊገጥመው ያስፈልጋል ብሎ ግንቦት 7 ያምናል፡፡

ግንቦት7 ከኢትዮጵያ ህዝብና ከሌሎች ለዴሞክራሲ፣ ለአንድነት ለፍትህና ለነጻነት ከቆሙ ሃይሎች ጋር በመተባበር ይህንን አቅም በአጭር ግዜ ውስጥ መገንባት ይቻላል ብሎ ያምናል፡፡

> እንዴት ተደርጎ የሚል ጥያቄ ካለዎት
> አይቻልም የሚል የአርግማን መልእክት ማስተላለፍ ካስፈለገዎ
> ግንቦት ሰባቱ እደጊ ተመንደጊ ዘር ይውጣልሽ ብለው ለመመረቅ ከፈለጉ
> እንዴት ልርዳህ ላግዝህ ብለው የሚጨነቁ ከሆነ

ከእዚህ በታች በተጠቀሱት ሃገሮች በተዘጋጁ ስብሰባዎች ይገኙ፡፡ ይካፈሉ፡፡

ተናጋሪዎች አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ፣ አቶ ሙሉነህ ኢዮኤል

ሃገር/ከተማ	Los Angeles, USA
ቀን	Sunday 20th July 2008
ሰአት	2:00pm Info Line: 703 595 6413
መሰብሰቢያ አዳራሽ	Aroma Wilshire Center, Sky Hall, 3680 Wilshire Blvd
(Free Parking)	No 501, Los Angeles, CA 90010

ሃገር/ከተማ	Las Vegas, USA
ቀን	Wednesday 23rd July 2008
ሰአት	6:00pm
መሰብሰቢያ አዳራሽ	Meskerem Restaurant